# ኢትዮጵያችን

*የአንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ (ኢትዮጵያችን) ልሳን*

ኢትዮጵያችን ቅጽ 5 ቁጥር 2 ኅዳር 24 ቀን 2 ሺህ 13 ዓ.ም.

## ድላችንን ለማጣጣም . . .

*የድምጽ ቅጂውን ለማድመጥ እዚህ ይጫኑ* (https://www.youtube.com/watch?v=3SRIrRV9OcM )

የ27 ዓመቱ ነቀርሳ አከርካሪው ተመታ። የሀገራችን ቀጣይ ጉዞ ከማውሳት በፊት ምንም ይሁን ምን ወያኔ/ህወሓት በመቀበሩ ኢትዮጵያችን እንኳን ደስ አለሽ። ሊበትኑሽ ያሴሩ ተበተኑ። ሊከፋፍሉሽ እንቅልፍ ያጡ ተከፋፍለው አሸለቡ። ሰንደቅ ዓላማሽን ያዋረዱ ተዋረዱ። ታሪካዊ ቅርሶችሽን ድንጋይ ያሉ ድንጋይ ተጫነባቸው። ጦርነት እንሠራለን ያሉ ተሠራባቸው። "ተራራ ያንቀጠቀጡ" ተንቀጠቀጠባቸው፣ የቀን ጅቦች ከጉድጓድ መሸጉ፣ የህውሓት ጎማ ተነፈሰ። ያሸለበ ጀግና "እምቢኝ ለሀገሬ" ጨፈረባቸው። "ዋይ! ዋይ! ወያኔ" ተጨፈረባቸው። ሀገር አራቁተዋልና ይበላቸው። ዜጎቻችንን አርደዋልና መሃት ወረደባቸው። ቤተ ክርስቲያን አቃጥለዋልና ወላፈኑ በላቸው። ኢትዮጵያዬን ላለ፣ ሕዝቤን ላለ ለወያኔ/ህወሓት ግፍና በደል መቀበር ሲያንሰው ነውና እንኳን ደስ አላችሁ መልዕክታችን ይድረሳችሁ።፡

የ32 ወራቱ የለውጥ ሂደት አስጨፍሮን ሳያበቃ፤ አስተክዞን፣ ወራት እየጠበቀ የሚከሰተው የአማራ ፍጅት አሳብዶን፣ ኢትዮጵያችንን ስናስብ ተስፋችን ተሟጦ፣ ሀገር ለማዳን ወኔያችን ታሥሮ፣ መስቀለኛ መንገድ ላይ የነበረችው ኢትዮጵያችን ዛሬ የድሏን መጀመሪያ በጀግና ሠራዊቷና ሕዝቧ ተጋድሎ ተቀዳጅታለች። ለአለፉት 27 ዓመታት ወያኔ/ህወሓት ከሀገራችንና ከሕዝባችን ጫንቃ ላይ የምናስወግድበት መላውና ዘዴው እስኪጠብብን ድረስ ተሰቃይተናል፡፡ ቀጣይ ሂደቱን አሁንም አምላክ የተሳካ ያድርግልን እያልን ክቡር ጠቅላይ ምኒስትር ዶክተር ዐብይ አሕመድ ወያኔ/ህወሓትን ድባቅ በመምታት ላሳዩትና ላስመዘገቡት ወታደራዊ ድል ምስጋና ሊቸራቸው ይገባል። በወያኔ/ህወሓት ላይ የተገኘው ወታደራዊ ድል የጀግናው መከላከያ ሠራዊታችን አኩሪ ተጋድሎና በጥቅሉ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሙሉ ተሳትፎ ውጤት በመሆኑም ይህ ነቀርሳ ቡድን እንዳያንሰራራ ተደርጎ መቀበር ይኖርበታል። ህወሓት የተባለ ድርጅት ከአራት አሥርተ ዓመታት በፊት በፀረ ኢትዮጵያ ማጭበርበሪያ ፖሊሲዎች ሲነሳ ሕዛባችን በደርግ ስለተማረረ የሥልጣን በሩ እንደተመቻቸለት ማስታወስ ያስፈልጋል። በአሁኑ ሰዓት በሥልጣን ላይ በነበረበት ጊዜ ብዙ ሀብት እንዳግበሰበሰና በፀረ ኢትዮጵያና በዘር ጥላቻ የታወሩ ብዙ ተከታዮች ያሉት አሸባሪና ወንጀለኛ ድርጅት ስለሆነ ፋታ ከተሰጠው እንደ እባብ አፈር ልሶ ሊነሳ ስለሚችል ሊያመጣ የሚችለውን መዘዝ በሚገባ መገንዘብ ይገባል።

የኅዳር 19 ቀን 2013 ዓ.ም. የድል ዜና የህወሓት ጁንታዎችን ብቻ ሳይሆን ህወሓት የሚባል ድርጅት የመቀበሩ ብሥራት መሆን ይገባዋል። ይህ የወንበዴ ቡድን አሸባሪነቱን መንግሥት መቀበልና ማወጅ ይኖርበታል። ከ1983 ዓ.ም. ጀምሮ በግፍ ለታረዱ፣ ለተጨፈጨፉ ዜጎቻችን በአለፉት ሁለት ዓመታት ደግሞ አንድ አማራ ዘር ላይ ባነጣጠረ ለተካሄደው ጭፍጨፋ ይህ ቡድን በአሸባሪነት ተፈርጆ በዘር ማጥፋት ወንጀል መጠየቅ ይኖርበታል። በቀጣይነት ይህ የወንበዴ አገዛዝ በኢሕአዴግ ስም በሀገራችንና በሕዝባችን ላይ ላደረሰው ወንጀልና የወንጀሉ አስፈጻሚ ሕግጋት ላይ የጠቅላይ ምኒስትር ዶክተር ዐብይ አሕመድ አመራር ያለምንም ማመንታት ቆራጥ አቋም መውሰድ ይኖርበታል።

በህወሓት ላይ የተገኘውን ሕዝባዊ ድል ለማጣጣም ከተፈለገ፦

1. የክልል ልዩ ኃይል የሚባሉ ወታደራዊ ተቋማት በሙሉ ፈርሰው የሀገሪቷ ጦር አሁን የአለው መከላከያ ኃይል መሆኑን ማወጅ
2. በዘር የተደራጁ የፖለቲካ ድርጅቶች በሙሉ ማፍረስና ከእንግዲህ ዘር/ቋንቋ/ሃይማኖትና ጾታን ተገን ያደረገ የፖለቲካ ድርጅት ክልክል መሆኑን በሕግ መደንገግ
3. ሙሉ በሙሉ ዘርንና/ቋንቋን ተገን ያደረገ የግዛት አከላለል በሕግ ማገድ
4. የእነዚህ ሁሉ ዋና ሥራ አስፈጻሚ የሆነውን የህወሓት ሕገ-መንግሥትን በአዋጅ መሻር

ህወሓት ጥቅምት 24 ቀን 2013 ዓ.ም. በመከላከያ ሠራዊቱ ላይ የፈጸመው ዘግናኝ ጭፍጨፋ የጦርነቱ መነሻ ቢሆንም ጠቅላይ ምኒስትር ዶክተር ዐብይ አሕመድ በአገዛዝ ዘመናቸው የደረሰው የዘር ፍጅትና ቤተ ክርስቲያንን ጨምሮ የንብረት ውድመት ቀዳሚ ተጠያቂ ህወሓት ቢሆንም ሌሎች ኃይሎች እንደ ኦነግ ሸኔ ዓይነት እንዳሉ ተገንዝበው ለዚህ ሁሉ ቀውስ መንግሥታቸውን የከተተው ህወሓት ኢትዮጵያን ለመበታተንና ለመከፋፈል የተጠቀመበት ሕገ-መንግሥት ጊዜ ሳይሰጠው ይቀየር ዘንድ በአሁኑ ወቅት ያዳበሩትን ሕዝባዊ ድጋፍ ከወታደራዊ ጥንካሬያቸው ጋር አጣምረው ይጠቀሙበት ዘንዳ ምክር ቤቱን ማወያየት ይጠበቅባቸዋል።

ቀናነቱ ካለ ኢትዮጵያ ሀገራችን ሕዝብ የሚመክርበት ትውልድ ተሻጋሪ ሕገ-መንግሥት እንዲረቀቅ ምክር ቤቱ ሊያመቻች ይችላል። በዚህ ሂደት እራሳቸው ጠ/ሚሩ የሚመሩት ብልጽግና ፓርቲ ጨምሮ ሁሉም የፖለቲካ ድርጅቶች ከዘር አደረጃጀት በጸዳ መልኩ እንደገና መዋቀር ይኖርባቸዋል። በተጨማሪም የሀገሪቷ አስተዳደራዊ ክልል በባለሙያዎችና በሚመለከታቸው አካላት በሚደረግ ጥናትና ምክክር ዘርና ቋንቋን ሳያማክል የማዋቀር ሥራውን ለመጀመር ጥናት ማካሄድ ያስፈልጋል።

ከላይ የጠቀስናቸው ጉዳዮች ያለምንም ማቅማማት የተገኘው የጦርነት ድል "ኢትዮጵያዊ ድል" እንዲሆን ከተፈለገ ሳይውል ሳያድር ተግባራዊ መሆን ይገባቸዋል። ህወሓትን ለመቅበር ደሙን ያፈሰሰው መከላከያ ኃይልና የአማራ ልዩ ኃይል በወያኔ መቃብር ላይ ያብብ ዘንድ ከተፈለገ ኢትዮጵያዊነት ከፍ! ማለት ይኖርበታል። ዛሬ በእርግጠኝነት መናገር የሚቻለው በተለያየ ጊዜ ከደረሰው የዘር ፍጅት በተለይ ደግሞ የቅርቡ ማይካድራ አማሮች ላይ የደረሰው አሳዛኝ እልቂት መቼም እንዳይደገም መፍትሄው ዘረኝነትን ከሥሩ መንቀል መሆኑን ሕዝብ የሚቀበለው ነው። ከእንግዲህ አማራ እየታረደ "አቢቹ" ሊባል ከቶም አይደፈርም። ቤተ ክርስቲያን እየተቃጠለ ለመንግሥት ሊጨበጨብ አይቻልም፡፡ በቀላል ቋንቋ ማብቃት አለበት፣ በቅቷልም። *<u>የወያኔ ሕገ መንግሥት የሙቀት መለኪያው የዘር ፍጅት ነውና ከፈጣሪው ህወሓት ጋር ወደ መቃብሩ መከተት ይኖርበታል።</u>*

የጠቅላይ ምኒስትር ዶ/ር ዐብይ አሕመድ አመራር በዚህ ጦርነት ላይ የተቀዳጁት ድል አስመስግኗቸዋል፣ ወደ ጥርጣሬ እያሽቆለቆለ የነበረውን ሕዝባዊ ድጋፋቸውን ዳግም አድሰውታል። ይህ ጦርነት ለእራሳቸውም ትምህርት ሊሆናቸው ይገባል። 27 ዓመት ሙሉ የተቀጠቀጠውና የተሰቃየው የኢትዮጵያ ሕዝብ በተለይ አማራው በዚህ ጦርነት ላይ ያስመዘገበው ተጋድሎ ኢትዮጵያ ያለ አማራ፣ አማራ ያለ ኢትዮጵያ ባዶ መሆናችንን ነው። ከእንግዲህ ወልቃይትና ጠገዴን "በሕገ-መንግሥቱ መሠረት" የትግራይ ክልል አድርገን እንጓዛለን ማለት አይታሰብም። ከእንግዲህ አገዛዙ "የእኛ ተራ ነው" ብለው ለቋመጡ የኦነግ አመራሮች እድል መስጠት ወያኔ/ህወሓት እንደገና እንዲያንሰራራ በሩን በመክፈት በጦርነቱ የፈሰሰውን ደም ዋጋ ማሳጣት ይሆናል። *<u>በጦርነት ያገኘነውን ድል በድርድር መልሰን መስጠት የለብንም።</u>* ከእንግዲህ በህወሓት ምትክ ሌላ የዘር ድርጅት ትግራይን እንዲያስተዳድር አድርጎ ዘረኝነትን ለማስቀጠል መሞከር ለሌላ እልቂት ጥይት ማቀባበል፣ ቆንጨራና ገጀራ መሳል ነውና ሊታሰብበት ይገባል፡፡ ህወሓት እንደ ድርጅት እንዳያንሰራራ ገና ብዙ ሥራ ይጠበቃል። እንደ ሸረሪት ድር በየተቋሙ የተሰገሰጉትን የዚህ ወንበዴ ቡድን አባላትን ማጥራት ብዙ ሥራ ይጠይቃልና ምንም ዓይነት ቀዳዳ መስጠት የለበትም። ከሁለት ዓመት በላይ የተደረገላቸው ትዕግስትና የይቅር ባይነት ስሜት ምላሻቸው የሀገር መከላከያ ሠራዊታችንን በተኙበት በማረድ ማንነታቸውን አስመስክረዋል። ለሚያውቃቸው በእንፍሽፍሽ ታሪካቸው የራሳቸውን ተጋዳዮች ያረዱትን ነው የደገሙት። በረቀቀ ዜዴ የህውዜን ሕዝብ ላይ ያደረሱትን ጭፍጨፋ ለሚያስታውስ የማይካድራ እልቂት የማንነታቸው መገለጫ ነውና የግድያና የወንጀል ድርጊታቸውን ነው የደጋገሙት። ወያኔ በዚህ ጦርነት አሸናፊ እሆናለሁ ትዕቢቱ ቢሳካለት መላ ኢትዮጵያ ማይካድራ እንደምትሆን አንጠራጠር። የኢትዮጵያ ሕዝብ በወያኔ/ህወሓት ላይ የተቀዳጀውን ድል ለማጣጣም ከተፈለገ ከእንግዲህ አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ሆነን ኢትዮጵያን የማስቀጠል ግዴታችንን መወጣት ይኖርብናል። በመቶ ሺህ የሚቆጠረውን የወያኔ ሠራዊት ለማክሰምና ህወሓት ዳግም እንዳያንሰራራ አባላቱን ኢትዮጵያዊነት ለማስጨበጥ በትግራይ የተጠናከረ ፖለቲካዊ ሥራ መሠራት ይኖርባታል።

በዚህ ጦርነት ወደ ሱዳን የተሰደዱ ሕጻናት፣ እናቶች፣ አዛውንቶች፣ ቤተሰቦች፣ 27 ዓመት ሙሉ የተነገደባቸው የትግራይ ምስኪኖች ተመልክተናል። እንደተፈራው ባይሆንም በጦርነቱ ወላፈን ሕይወታቸውን ያጡም የዚሁ የዘረኝነት አገዛዝ ሰለባዎች ናቸው። ይህንን ድል ከሀገርና ሕዝብ ጋር ለማጣጣም ከተፈለገ፣ አዲስቷን ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ለመገንባት፣ የእድገትና ብልጽግና ጎዳና እውን እንዲሆን ከተፈለገ ጠ/ሚር ዶ/ር ዐብይ አሕመድ በሙሉ ልቦናዎ ሕዝቡን ይመልከቱ። የ27 ዓመት የወያኔ አገዛዝና ሕገ-መንግሥት ኢትዮጵያ ሳትበታተን ጦርነቱ በድል አድራጊነት መደምደሙ እድለኞች ነን፤ ለዚህ ደግሞ ከአኩሪው መከላከያ ሠራዊትና ከሕዝባችን ጋር የአምበሳውን ድርሻ ጠ/ሚሩ ይወስዳሉ።

ኅዳር 22 ቀን 2013 ዓ.ም. ጠ/ሚሩ ከተወካዮች ምክር ቤት አባላት ለበቀረቡላቸው ጥያቄዎች በሰጡት ማብራሪያ ወሳኝና መሠረታዊ ጉዳዮች ላይ ማብራሪያ ከመስጠትና ጉዳዩን ከመመልከት አልፈዋቸዋል። ጠ/ሚሩ በአለፉት 32 ወራት የደረሰባቸውና የተወጡት አደገኛ ጉዞ እንደተጠበቀ በአሁኑ ወቅት ዋናውን የሀገሪቷ ነቀርሳ ወያኔ/ህወሓት በኢትዮጵያ መከላከያ ኃይል ብቃትና ጥንካሬ እንዲሁም በሕዝባችን ተጋድሎ ወደ መቃብሩ እየተከተተ ነው። ይህ የሚያሳየው በአንድ በኩል የሠራዊቱን ጥንካሬ ሲሆን በሌላ በኩል የጠ/ሚር ዶ/ር ዐብይ አሕመድ አገዛዝ በመጠናከር ዋናውን እንቅፋት ማስወገዱን ሲሆን ርዝራዡና ሌሎች ቡድኖች አሁንም ሕዝባችን ከመከላከያ ሠራዊቱ ጋር በመሆን እንደሚያስወግዳቸው መተማመን ይቻላል። ይህ ግና ተግባራዊ የሚሆነው ለኢትዮጵያ የግዛት

**ሉዓላዊነትና ለሕዝቧ አንድነት ሲባል በመሆኑ ይህንን ሕዝባዊ አንድነት የሸረሸረውና የከፋፈለው የወያኔ ዘረኛ ሕገ-መንግሥት ይቀየር ዘንድ ለመመካከር ካልተዘጋጁ ነገሮች ሊበላሹ እንደሚችሉ መገመት ብቻ ሳይሆን ይበላሻሉ።**

**በዚህ 32 ወራት የለውጥ ጉዞ ሕገ-መንግሥቱን ተገን ተደርጎ ለተሠሩ የዘር ፍጅቶች በወያኔ/ህወሓት/ኦነግ ሸኔ ተሳቦ "ይሁና" ብለናል። በቀጣይነት የህወሓት ዘረኛ ሕገ-መንግሥትና ዘርንና ቋንቋን ተገን ያደረገ አከላለል ለሚያመጣው ቀጣይ ጣጣ ወደ ተረኛ ተጠያቂነት ከመዘፈቅ በፊት አሁን የተገኘውን ድል ለማጣጣም ከተፈለገ ሕዝብንና ሠራዊቱን ይዞ ጠንካራ የፖለቲካ ውሳኔ እንደሚያስፈልግ እንጠቁማለን።**

**ሀገር በዐብይ እንድትኮራ ዘረኝነትና የወያኔ ሕገ-መንግሥት ከህወሓት ጋር ይቀበሩ!**

**ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!!!**

**ፈጣሪ ኢትዮጵያንና ሕዝቧን ይጠብቅ!!!**

**አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ**

**ኅዳር 24 ቀን 2013 ዓ.ም. (December 02, 2020)**

**ማሳሰቢያ ፡**

- ውድ ወገኖቻችን ይህንን «አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ» «***ኢትዮጵያችን***» ልሳን በተለይ በሀገር ቤት ኮምፒዩተር የማግኘት ዕድል ለሌላቸው በማባዛት ታሰራጩት ዘንድ ቀና ትብብራችሁን በትህትና እንጠይቃለን።
- «አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ» መስከረም 8 ቀን 2009 ዓ.ም. እራሱን ይፋ ያደረገ ሕዝባዊ ድርጅት ሲሆን የንቅናቄውን ማንፌስቶና ፕሮግራም www.ethiopiachen.org ከሚለው ድረ ገጻችን ማግኘት ትችላላችሁ።

ኢሜል ፡ ethiopiachen2009@gmail.com
ድረ ገጽ ፡ www.ethiopiachen.org , www.ethiopiachen.com
ምሥለ ገጽ ፡ 1H1H Ethiopiachin